

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከዲሴምበር 11-20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

# እንዲሁም

# ከዲሴምበር 21-31/2025 እና ከጃንዋሪ 1-10/2026

# የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት ለበጋ ዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ገጽታ ነበራቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ሶማሌ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ10 ሚ.ሜ በላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ኮምቦልቻ 11.1፣ ደበረ ማርቆስ 12.5፣ ድሬዳዋ 17.3፣ ጅማ 59.2፣ ነቀምት 21.3፣ አማን 27.5፣ አርጆ 10.4፣ 16.4፣ ባቲ 36፣ ጭፍራ 10.2፣ ጭራ 14፣ ፉኙዶ 21.4፣ ጋምቤላ 21.1፣ ገቲራ 18.3፣ 11.3፣ ወሊሶ 12.6፣ ሆሳና 15.2፣ እምድብር 13.3፣ 13.8፣ ጅንካ 18.8፣ 18.2፣ 48.8፣ ካቺሴ 20፣ ማጂቴ 13.2፣ ማጂ 12.8፣ ማሻ 50.4፣ ሞሌ 36.4፣ ሰኮሩ 10.6፣ ሲሪንቃ 10.2፣ ተርጫ 17.2፣ ያቤሎ 15.1፣ቡልቂ 20.7፣ 10.7፣ 17.6፣ 20.7፣ 16.4፣ ደበረ ሲና 16.8፣ ፎጉ ሌቃ 10.5፣ 11.5፣ ሃርሲሲ 21፣ ሆርዶዮ 12.9፣ ቅዳሜ ገበያ 18.6፣ ኩሚ 11.8፣ መሆኒ 12፣ መልካ ጀባዱ 12.8፣ መርሳ 16፣ ሲቦ 16.3፣ ትንሹ መጢ 14.3፣ መንደር አስራ አንድ 16፣ 11፣ ያዮ 26.2፣ ወንዶ ገነት 10.1፣ 15.2 እንዲሁምኮረም 13.1 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በአስራ ሶስት (13) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ የሆነ መካከለኛ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡

Ethiopian Meteorology Institute





ምስል፡1 ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ጥቂት የቦረና እና ምስራቅ ቦረና የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የዳዋ እና ሊበን ዞኖች ላይ ከ6-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

በሌላ በኩል ምስራቅ ጎጃም፣ የሰማን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋ ዞን፤ የማኦ ኮሞ ዞን፤ የቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ፈንቲ፣ ሀውሲ፣ የማሂ እና ሀሪ ዞኖች፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፤ ምዕራብ ትግራይ፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ ዞን፣ ላይ ከ11-40 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እሰከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ከ2-5 ቀናት ያህል ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ ኦሮሚያ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ መደበኛ እና ከመደበኛዉ በላይ፤ የደቡብ ሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ከመደበኛ በታች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር

በሌላ በኩል የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናቶች ተስተዉሏል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሸየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም ሐሮማያ 3.8፣ 4.0፣ 4.2፣ አለም ከተማ 4.8፣ 4.5፣ አምባ ማሪያም 4.8፣ 4.5፣ ቡሂ 4.8፣ 4.0፣ 3.6፣ 4.0፣ 4.6፣ ጨለንቆ 2.0፣ -1.0፣ -3.0፣ -2.0፣ -1.0፣ 2.1፣ 3.3፣ 3.5፣ ደብረ ብርሃን 4.6፣ 3.8፣ ዳባት 4.3፣ ቢሾፌቱ 4.0፣ 4.2፣ ጅግጅጋ 3.5፣ 4.0፣ ኮረም 2.5፣ 4.0፣ 4.0፣ 2.0፣ ቁሉቢ 4.1፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.8፣ እንዲሁም ወግል ጤና 4.6 በዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል (ምስል 2)፡፡





ምስል 2፡ ከዲሴምበር 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የተመዘገበባቸዉ ስፍራዎች

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1.2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት የዲሴምበር ሁለተኛው አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የነበረው እርጥበት በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ በሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ሶማሌ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት ገንቢ ሚና ነበረው። በሌላም በኩል በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አሉተዊ ተፅእኖ ነበረው። እንዲሁም በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለው ደረቃማ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበረው የደመና ሽፋን መጨመር ጋር ተያይዞ በደጋማ አካባቢዎች ላይ የነበረው ቅዝቃዜ እንዲቀንስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ከዲሴምበር ሁለተኛ አሥር ቀናት በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በመካከለኛው አባይ፣ በታችኛ ገናሌ ዳዋ፣ ሰሜናዊ ታችኛው አዋሽ እንዲሁም በጥቂት ላይኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች የተሻለ የገፀ ምድር የውሀ ፍሰት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እና የተፋሰሶችን የስነ-ምህዳር ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በአንጻሩ በአብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ተከዜ፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ እና አይሻ ተፋሰሶች በአብዛኛው ደረቅ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም ተፋሰሶች ውስጥ ያለው ደረቅ የአየር ሁኔታ የገፀ ምድር ውሀ ፍሰት በመቀነስ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 5)።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በዲሴምበር የሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚገባው ደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅ፣ መካከለኛው እና ደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አንጻዊ ጥንካሬ ይኖረዋል (ካርታ 7)፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ውርጭ የማስከተል ጥንካሬ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡


## 2.1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የዲሴምበር ሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የደቡብ ኦሮሚያ፤ ሲዳማ ክልል፤ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ እና የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በመሆኑም በደቡብ ኦሮሚያ የሚገኙ የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ እንዲሁም የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ነጎብ፣ ኤረር፣ እና ጃረር ዞኖች ላይ የሚገኘዉን ዝናብ በአግባቡ በመሰብሰብ ሊኖር የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ መቀነስ ያስፈልጋል (ካርታ 6)፡፡

በሌላ በኩል ከሚኖረው የደመና ሽፋን ላይ በመነሳት በጥቂት የሰሜን እና ደቡብ ጎንደር፣ በሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፤ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ የምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሊባቦር፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬ ደዋ እና ሐረሪ፣ የሲቲና ፋፋን ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎች ቀናቶች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የደቡብ ምዕራብ እና የምስራቅ አካባቢዎች ከቀላል እእስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 21-31, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 21-31, 2025 የሚኖረዉ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጥቂት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሊ | ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ንጎብ፣ ኤረር እና ጃረር ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |

| በጥቂት አከባበቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች | | |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | የምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን፤ ምዕራብ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን እና ደቡብ ጎንደር፣ የምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጥቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌዲዮ፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| | አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

Ethiopian Meteorology Institute

በሚቀጥሉት የዲሴምብር ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ አየር እንደሚቀጥል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም ከሳምንቱ አጋማሽ በኋላ በሰሜን፣ ምስራቅ፣ መከከለኛዉና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ምስል 3)።




ምስል፡3 ከዲሴምበር 21-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከአራት (4) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የሚመዘገብባቸው ስፍራዎች

## 2.2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀን የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሰፍኖ የሚታይበትና ከዚሁ ጋር ተያይዞም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ ዝናብ ይዘንባል፡፡

Ethiopian Meteorology Institute

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀን ቀናት ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ አየር እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን፣ ምስራቅ፣ መከከለኛዉና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ፣ በመካከለኛዉ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

በሌላ በኩል በጸሀይ ኃይል ታግዘው የሚፈጠሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አሮሚያ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና ጥቂት የደቡብ ሶማሌ ዞኖች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 2.3 እ.አ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በአብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ፣ የሰብል ስብሰባ እና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት እየተከናወነ በሚገኝባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ይጠበቃል። በአንጻሩ ግን በተወሰኑ የመኸር አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ያገኛሉ። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በጥቂት የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ መተግበር ያስፈልጋል።

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ንጎብ፣ ኤረር እና ጃረር ዞኖች | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገትና ፍሬ ለማፍራት<br>• ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን<br>• ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የእንስሳት መኖ ከሰብል ተረፈ ምርት ማሰባሰብ እና ማከማቸት |
| ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች እና ሁሉም ሲዳማ ክልል ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገትና ፍሬ ለማፍራት<br>• ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የእንስሳት መኖ ከሰብል ተረፈ ምርት ማሰባሰብ እና ማከማቸት |
| **በጥቂት ቦታዎቻች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚጠበቅባቸው(የመኸር ሰብል አምራች ዞኖች)** | | | | |
| የምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ የምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን፤ ምዕራብ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ሰሜን እና ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ ደቡብና የሰሜን ወሎ፣ሰሜን ሸዋ፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ማዢ፣ ሀሪ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ ፣ ጋቢ ፣ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ በጥቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌዲዮ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ | አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • በአፈር ውስጥ በተከማች እርጥበት ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የጥራጥሬ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት<br>• የውርጭ ስጋት መቀነስ | • የደረሱ ሰብሎች ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ<br>• በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመረ | • የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል<br>• የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን<br>• አልፎ አልፎ የውርጭ ክስተት በሚጠበቅባቸው አንዳንድ አካባቢዎች በሰብሎችና በመስኖ በሚበቅሉ አዝዕርቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ |

## 2.4 እ.አ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት ዲሴምበር ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት **የባሮ አኮቦ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች** መጠነኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን የተቀሩት በአብዛኛው ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ። በመሆኑም  የዘርፉ አካላት የቀረቡትን ተፋሰስ ተኮር የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም አሉታዊ ተፅኖዎች እንዲቀንሱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር

| የውሀ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በላይኛ እና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ጥቂት በመካከለኛ እና ታችኛው አባይ፣ በመካከለኛ ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት ላይኛው አዋሽ እንዲሁም በላይኛው ገናሌ ዳዋ | መካከለኛ የእርጥበት መጠን | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም ለመጠጥ ውሀ መጠነኛ የውኃ አቅርቦት መጠን መጨመር | • አንጻራዊ የትነት መጨመር | • ከብለት መጠበቅ<br>• ውሀን በተገቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የሚገኘውን ውሀ ከብክነት እና ከብክለት መጠበቅ<br>• የዉሀ መያዣዎች መከታተል እና የዉሀ አለቃቅ በተገቢ ሁኔታ መተግበር |
| በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን እና አይሻ፣ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • ወንዞች እና ሌሎች የውሀ አካለት በደራሽ ቆሻሻ አለመበከል<br>• የጎርፍ ናዳ አደጋ ስጋት መቀነስ | • የወንዞች እንዲሁም በሌሎች የዉሀ አካላት መጠን መቀነስ | • የዝናብ ውሀ ከጣራ እና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት መከላከል |